በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# ቅድስት ሥላሴ - ክፍል 1


## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com


***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ነሐሴ ፲፱ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም.

# ቅድስት ሥላሴ

## *መግቢያ*

- በዚህ ርዕስ ሥር ስለ ቅድስት ሥላሴ (እግዚአብሔር - አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ) ሦስትነትና አንድነት እንማራለን፡፡ ሥላሴን ቅድስት ብለን የምንጠራው ሴት ልጅ ወልዳ እንደምታስገኝ ሥላሴ ዓለማትን ፈጥረው ስላስገኙ ነው፡፡
- ብዙዎች ስለ ቅድስት ሥላሴ ያለውን ትምህርት እየሰሙ በእውነት ክርስቲያኖች በአንድ አምላክ ያምናሉ? የሚያምኑስ ከሆነ አብ፣ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ማለት ምንድር ነው? ብለው ይጠይቃሉ፡፡
- በተዛባ ግንዛቤም የተነሳ አንዳንድ ሰዎች ክርስቲያኖች ብዙ አማልክትን ያመልካሉ ብለው ይከሳሉ፡፡ የዚህም ምንጩ "ሥላሴ" የሚለውን ሦስት አማልክት ብለው ማሰባቸው ነው፡፡
- በክርስትና እምነት ይህ የተሳሳተ አመለካከት ነው፡፡ በክርስትና እምነት በብዙ አማልክት (Polytheism) ማምለክ የተከለከለ ነው፡፡
- የክርስትና እምነት ማዕከሉ በአንድ አምላክ ማመን (Monotheism) ነው፡፡
- ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ከትእዛዛቱ ሁሉ ፊተኛይቱ፡፡ እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው፥ አንተም በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም አሳብህ በፍጹምም ኃይልህ ጌታ አምላክህን ውደድ የምትል ናት፡፡ ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት፡፡" *ማር 12:29-30፡፡* ብሎ ነግሮናል፡፡
- ብዙዎቻችን ተተንትኖ ከተዘጋጀው ሥነ መለኮታዊ ጥናት ይልቅ ለጊዜያችን በሚመጥን መልኩ ተስተካክሎ አጠር መጠን ብሎ የቀረበን አስተምህሮ እንፈልጋለንና በዚህ አጭር ትምህርት የምንማረውም ስለ ሥላሴ - እግዚአብሔር ራሱን ለሰው ከገለጠበት አንጻር በመመልከት ነው፡፡

# ቅድስት ሥላሴ

- እግዚአብሔርን የሚመስለው ማንም የለም፡፡ እግዚአብሔር በኢሳይያስ አንደበት “እኔ አምላክ ነኝና፥ ሌላም የለምና የቀድሞውን የጥንቱን ነገር አስቡ እኔ እግዚአብሔር ነኝ እንደ እኔም ያለ ማንም የለም፡፡” *ኢሳ 46፡9* ብሏል፡፡
- እግዚአብሔር በሁሉ ነገር የተለየ የሚተካከለው የሌለ ነው፡፡ “እንግዲህ እተካከለው ዘንድ በማን መሰላችሁኝ? ይላል ቅዱሱ፡፡” *ኢሳ 40፡25፡፡*
- ዓለምን ሁሉ በውስጣቸው የሚገኘውንም ሁሉ የፈጠረ የሚመስለው የሌለ እግዚአብሔር ነው፡፡ “በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ፡፡” *ዘፍጥ 1፡1፡፡* እርሱንም የሚመስለው የለም፡፡
- እግዚአብሔር ከሰው ችሎታና ግምት የላቀ የመጠቀ ነው፡፡
- የእኛ በሆነው ጠባብ አእምሮ በተዳሰሰ ጥቂት ማብራሪያ እርሱንና መለኮታዊ አምላክነቱን ገልጦ ማስረዳት አይቻልም፡፡
- የእግዚአብሔር ሀሣቡ፣ መንገዱ፣ ዓላማው (እቅዱ) የሰው ከሆነው የተለየ ነው፡፡ “አሳቤ እንደ አሳባችሁ መንገዳችሁም እንደ መንገዴ አይደለምና ይላል እግዚአብሔር፦ ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል፥ እንዲሁ መንገዴ ከመንገዳችሁ አሳቤም ከአሳባችሁ ከፍ ያለ ነው፡፡” *ኢሳ 55፡8-9* እንዳለ፡፡
- ስለ እግዚአብሔር የምናውቀው ወይም ያወቅነው የገለጠልንን ያህል ብቻ ነው፡፡ ስለ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር የምናውቅ አይደለንም፡፡
- እግዚአብሔር አማላካችን ስለ ራሱ ያልገለጠልን ምስጢራት አሉ፡፡ ሊቀ ነቢያት ሙሴ “ምሥጢሩ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ነው የተገለጠው ግን የዚህን ሕግ ቃሎች ሁሉ እናደርግ ዘንድ ለእኛ ለዘላለምም ለልጆቻችን ነው፡፡” *ዘዳግ 29፡29፡፡*

# ቅድስት ሥላሴ

- በዙሪያችን ከሚገኙ ነገሮች ሁሉ የተለየ ከመሆኑ የተነሳ ስለ ርሱ በሰው ቋንቋ መናገርና ማስረዳት ከባድ ነው።
- ስለዚህ መለኮታዊ ነገርን ለማስረዳት ምሳሌዎችን መጠቀም ግድ ይሆናል። ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በትምህርቱ በርካታ ምሳሌዎችን ተጠቅሞ አስተምሯል። ቅዱስ ማቴዎስ እንደተናገረው ቢያንስ አንድ ምሳሌ ሳይጨምር አልተናገረም ነበር። "ኢየሱስም ለሕዝቡ ይህን ሁሉ በምሳሌ ተናገረ፤ በነቢዩም። በምሳሌ አፌን እከፍታለሁ፥ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የተሰወረውንም እናገራለሁ የተባለው ይፈጸም ዘንድ ያለ ምሳሌ አልተናገራቸውም።" _**ማቴ 13፡34።**_
- እነዚህ ምሳሌዎች ከሰማዕያኑ የዘወትር ሕይወት የመነጩ ናቸው። ስለ መለኮት የሚነገረውን እውነት የሚመስሉ ምሳሌዎች ወይም ማስረጃዎች ተሰጥተዋል። ይህም በግድግዳ ላይ ያለ ሥዕልን እንደ መመልከት ነው። ሥዕሉ ተፈጥሮን በቀጥታ የምንመለከትበት ባይሆንም ተፈጥሮን ግን ወክሎ መስሎ ያቀርባል። የሚወርድ ውሃ በሥዕሉ ላይ ብንመለከት ለመጠጣት እጃችንን አንዘረጋም። በሥዕሉ ላይ እሳት ቢኖር እውነተኛው እሳት ስላልሆነ በጥንቃቄ እጃችንን ዘርግተን የእሳቱን ነበልባል ሳያቃጥለን መንካት እንችላለን።
- ምሳሌ እንደ ሥዕሉ እውነትን ለማስረዳት ይቀርባል። ምሳሌ እውነቱን ለማስረዳት በጽሁፍም ሊቀርብ ይችላል። ነገር ግን እውነቱ አሁንም ከማንኛውም ምሳሌ በላይ ነው።
- "እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ።" _**ዮሐ 15፡1-27**_ በማለት ጌታችን የተናገረው "የእውነተኛ የወይን ግንድ" ምሳሌ ለቅድስት ሥላሴ ጥሩ ምሳሌ ሆኖ ሊቀርብ ይችላል። ሙሉውን ምዕራፍ ስናነብ ስለ ሦስቱም አካለት ያስተማረውን ትምህርት እናገኛለን።
- የተለያየ ዓይነት ዛፎች ስለሚገኙበት አንድ የአትክልት ሥፍራ እናስብ። አንዳንዶቹ ሥራቸው ከመሬት ጠልቆ የገቡ የተፈጥሮ ዛፎች ናቸው፤ ሌሎቹ ደግሞ ለአካባቢ ወይም ለቤት ማሳመሪያ እንዲሆኑ የተሠሩ ሥር የሌላቸው ሰው ሠራሽ ዛፎች ናቸው፤ ቀጥሎ የሚገኙት ዛፎች ደግሞ ቅርንጫፎች ቢኖሩአቸውም ሥር ግን የሌላቸው ናቸው፤ በማስከተልም ያሉት ከፕላስቲክ የተሠሩ ዛፎች ሲሆኑ በእነዚህ ሁሉ መካከል ግን እውነተኛ የወይን ዛፍ ይገኛል።

# ቅድስት ሥላሴ

- በዚህ በአእምሮ በታሰበ የአትክልት ሥፍራ እውነተኛውን ዛፍና ጥራቱን እንዴት ለይተን መወቅ እንችላለን? ወይም እውነተኛው ዛፍ ራሱን እንዴት አድርጎ መግለጥ ይችላል? ዛፉ ምንነቱንና ጥራቱን ለይተን ማወቅ እንዲያስችለን ራሱን የሚገልጥበት መንገድ ሊኖረው ያስፈልጋል፡፡
- ዛፍ ብቻ ሳይሆን ማንኛውም በዚህ ዓለም የሚገኝ ቁሳዊ ነገር ራሱን የሚገልጥበት መንገድ አለው፡፡ ለምሳሌ ፀሐይን ብንወስድ መኖርዋን በሚያረጋግጡላት ነገሮች (በክበቧ፣ በብርሃንዋና በሙቀትዋ) አማካኝነት ፀሐይ ስለመኖርዋ እንናገራለን፡፡ በነዚህም ወሳኝ በሆኑ መገለጫዎቿ አማካኝነት ፀሐይ ስለመኖርዋና ስለተጽእኖዋ ግልጽ ታደርጋለች፡፡ እነዚህ ሦስቱም በሁሉ ዘንድ የምትታወቅ የአንዷት ፀሐይ መገለጫዎች ናቸው፡፡ እነዚህም ሦስቱ የፀሐይ መገለጫዎች ባይኖሩ ፀሐይ ሐሳብ ብቻ የምትሆን ወይም የለችም ተብላ የምትቆጠር ነበረች፡፡
- እንደዚሁ ስለ እግዚአብሔር መኖርና እንሰማለን እናነባለንም፡፡ ይህ እውነት ግን እግዚአብሔር ራሱን ባይገልጥ ኖሮ ተራ ሐሳብ ወይም አጠራጣሪ እምነት ይሆን ነበር፡፡
- እግዚአብሔር ራሱን የገለጠበትና የሚገልጥበት የራሱ ብቻ የሆኑ ብቸኛ መንገዶች አሉ፤ ስለ ቅድስት ሥላሴ የምንለውም እውነት ዋና ምንጭም ይኸው ነው፡፡
- ስለ ሥላሴ በማወቅና በመረዳት እግዚአብሔር አለ እንላለን፡፡
- እግዚአብሔር ራሱን ብቸኛ በሖነ መንገድ ገልጧል፡፡
- ስለዚህ ስለ ቅድስት ሥላሴ ከቅዱሳት መጻሕፍት በምናደርገው ፍለጋ የሚከተሉትን እንመለከታለን፡፡

# እግዚአብሔር አብ

- ስለ ወይኑ ዛፍ ስናስብ ቀድሞ የሚታሰበን ሥሩ ነው። እውነተኛ ዛፍ ሥር አለው። ሥር የሌለው ዛፍ የለም። ካልሆነ ግን ቃል ወይም ሐሳብ እንጂ እውነተኛ ዛፍ ሊሆን አይችልም።
- ለእያንዳንዱም እንደዚሁ አባት አለው። አባት የሌለው በራሱ ያለና የሚኖር አስገኝ የሌለው "የሁሉ አባት" ግን ማነው? የሁሉ አባት እግዚአብሔር ራሱ ነው። እግዚአብሔርንም አባት ለማለት አብ ብለን እንጠራዋለን። እርሱም ከሦስቱ አካላት አንዱ ነው። ነገር ግን አባት ስንል ምን ማለታችን ነው?

1. *<u>የእግዚአብሔር ወልድ - የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ነው።</u>*

- ጌታችን እውነተኛ የወይን ግንድ ነኝ ብሎናል። ዮሐ 15፡1። ነገር ግን የማን ልጅ ነው? "ፈሪሳውያንም ተሰብስበው ሳሉ፥ ኢየሱስ፦ ስለ ክርስቶስ ምን ይመስላችኋል? የማንስ ልጅ ነው? ብሎ ጠየቃቸው።" ማቴ 22፡42።
- ጌታችን እንደ ሰው ከሥጋ አባት ተወልዶ ቢሆን ስለ ሥጋ አባቱ ይነገረን ነበር።
- ክርስቲያኖችም ሆኑ ሌሎች እግዚአብሔር አብ የኢየሱስ ክርስቶስ አባት እንደሆኑ ስለ ተለያዩ ምክንያቶች ያምናሉ።
- የማይታይ የማይመረመረው እግዚአብሔር (አብ) የእግዚአብሔር ወልድ የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በወይኑ ዛፍ ምሳሌ "ገበሬውም አባቴ ነው" እንዳለ በተለያዩ አጋጣሚዎች እግዚአብሔርን (አብ) "አባቴ" ብሎ ጠርቶታል።
- ቅዱስ ጳውሎስም እግዚአብሔር (አብ) "የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት" ብሎ ጠርቶታል። ካል ቆሮ 1፡3፣ ካል ቆሮ 11፡31፣ ኤፌ 1፡3፣ ኤፌ 3፡14።
- ኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር አብ የተገኘ ነው። ጌታችን ራሱም "ከአብ ወጥቼ ወደ ዓለም መጥቻለሁ፤ ደግሞ ዓለምን እተወዋለሁ ወደ አብም እሄዳለሁ።" ዮሐ 16፡28። ብሎናል።
- በትንቢትም "አንቺም ቤተ ልሔም ኤፍራታ ሆይ፥ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ፥ በእስራኤልም ላይ ገዥ የሚሆን ይወጣልኛል።" ሚክ 5፡2 ተብሎ ተነግሮናል።

# <u>እግዚአብሔር አብ</u>

- ጌታችን "ሕያው አብ እንደ ላከኝ እኔም ከአብ የተነሣ ሕያው እንደምሆን፥ እንዲሁ የሚበላኝ ደግሞ ከእኔ የተነሣ ሕያው ይሆናል።" *<u>ዮሐ 6፡57።</u>* ብሎናል።
- ከክርስቶስ እኩል የእግዚአብሔር አብን አባትነት እጋራለሁ የሚል አይኖርም። እግዚአብሔር አብ የኢየሱስ ክርስቶስ አባትነቱ በተፈጥሮ ሕግ እንደሚሆነው (በማግባትና በመውለድ) አይደለም።
- እግዚአብሔር መንፈስ ነውና ስለርሱ የምንናገረውም በመንፈሳዊ መንገድ ነው።

*<u>2. እግዚአብሔር የሁሉ አባት ነው</u>*

- እግዚአብሔር የሁሉ ፈጣሪ ነው። "ለሁላችን አንድ አባት ያለን አይደለምን? አንድ አምላክስ የፈጠረን አይደለምን? የአባቶቻችንን ቃል ኪዳን ለማስነቀፍ እኛ እያንዳንዳችን ወንድማችንን ስለ ምን አታለልን?" *<u>ሚል 2፡10።</u>* ብሎናል።
- ሊቀ ነቢያት ሙሴም እስራኤልን "ደንቆሮ ብልሃተኛም ያልሆንህ ሕዝብ ሆይ፥ ለእግዚአብሔር ይህንን ትመልሳለህ? የገዛህ አባትህ አይደለምን? የፈጠረህና ያጸናህ እርሱ ነው።" *<u>ዘዳግ 32፡6።</u>* ብሎናል።
- ነቢዩ ኢሳይያስም "አሁን ግን፥ አቤቱ፥ አንተ አባታችን ነህ እኛ ጭቃ ነን አንተም ሠሪያችን ነህ፥ እኛም ሁላችን የእጅህ ሥራ ነን።" *<u>ኢሳ 64፡8።</u>* ብሎናል።
- ቅዱስ ጳውሎስም "ለእኛስ ነገር ሁሉ ከእርሱ የሆነ እኛም ለእርሱ የሆንን አንድ አምላክ አብ አለን፥ ነገር ሁሉም በእርሱ በኩል የሆነ እኛም በእርሱ በኩል የሆንን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን።" ቀዳ ቆሮ 8፡6። እንዲሁም "በእርሱ ሕያዋን ነንና እንንቀሳቀሳለን እንኖርማለን።" *<u>የሐ ሥራ 17፡28።</u>* ብሎአል።

# እግዚአብሔር አብ

## *3. እግዚአብሔር የሚያምኑበት አማንያን ሁሉ አባት ነው*

- እግዚአብሔር ስለወደደንና ስለራራልን እኛም አምላክነቱንና አባትነቱን አምነን በጥምቀት በመወለዳችን አባታችን ይባላል፡፡ "በበጎ ፈቃዱ እንደ ወደደ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን፡፡" ኤፌ 1፡5፡፡
- ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጁ ነው ብለን ለምናምን ሁሉ እግዚአብሔር አባታችን ነው፡፡ "ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፡፡" ዮሐ 1፡12፡፡

*ማጠቃለያ*

*እግዚአብሔር አብ*

1. የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ሲሆን ኢየሱስ ክርስቶስም አንድያ ልጁ ነው፡፡
2. ሁሉን ፈጥሯልና የፍጥረታት ሁሉ አባት ነው፡፡
3. በርሱ የሚያምኑ ሁሉ አባት ነው፡፡
4. የሕይወት ምንጭ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስም የወጣው (የሠረጸው) ከእርሱ ነው፡፡ ዮሐ 15፡26፡፡

- በሐዲስ ኪዳን በእግዚአብሔር አብ ማመን ማለት በአንድ እግዚአብሔር ማመን ማለት ነው፡፡ አባት የሚለው የሚምታታባቸው የእግዚአብሔርን አባትነት ከሥጋ አባትነት ጋር ከማገናኘት መቆጠብ ይገባቸዋል - አባትነቱ የሥጋ አባትነትን አያመለክትምና፡፡
- *… እግዚአብሔር ወልድ፣ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፣ አንድነት በሦስትነት … ይቀጥላል፡፡*

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org